QuickNotes mcps

**ሴፕቴምበር 19/2018 ፈጣን መልእክት/QuickNotes**

**የወላጅ አካዴሚ አዳዲስ አውደጥናቶችን/ዎርክሾፖችን ይሰጣል**

ፎል ላይ ለሚካሄደው የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የፓረንት አካደሚ/MCPS Parent Academy ምዝገባ ተጀምሯል። እነዚህ በነፃ የሚሰጡ አውደጥናቶች/ዎርክሾፖች ወላጆች ልጆቻቸው በት/ቤት ውጤታማ እንዲሆኑ ለመርዳት የሚያስችላቸው ጠቃሚ የሆነ እውቀት እና መገልገያዎችን ይሰጣል።

በፎል ወቅት የሚካሄደው የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ፓረንት አካደሚ/MCPS Parent Academy ሴፕቴምበር 24 ይጀመራል። ወላጆች እና የማህበረሰብ አባላት በእነዚህ መረጃዎችን/ኢንፎርሜሽን፣ ሪሶርስስ/መገልገያዎችን እና ፍንጮችን በነጻ የሚሰጡ አውደጥናቶች/ዎርክሾፖች ላይ እንዲሳተፉ ተጋብዘዋል። የኮሌጅ እና የሥራ እቅዶችን ጨምሮ፣ በተለያዩ ርእሶች ስለ ትምህርት የጥናት ዘዴዎች/ስልቶች፣ ሳይበርሴፍቲ እና ማህበራዊ ሚዲያ፣ እና መልካም ግንኙነት ላይ በዚህ ወቅት የሚካሄዱ አውደጥናቶች/ዎርክሾፖች እንዳያመልጥዎት።

የወላጅ አካዴሚ ዎርክሾፖች ነፃ ናቸው። ጥያቄ ሲቀርብ የህፃናት/ልጆች እንክብካቤ እና የትርጉም አገልግሎት ይሰጣል። የኮርሶች የተሟላ ዝርዝር በ [Parent Academy/የወላጅ አካዴሚ ድርጣብያ] ላይ ይገኛል።

እንዲሁም፡-

ስለ ኮሌጅ እና እንዴት እንደሚከፈልበት ማገናዘብ ጀምራችሁ ከሆነ፣ በፎል ወራት በሙሉ በMCPS ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በነፃ በሚካሄደው የ [ፋይናንስ እርዳታ ዎርክሾፖች] ተገኝታችሁ ተማሩ። በእነዚህ ክፍለጊዜያት፣ ወላጆችና ተማሪዎች የፋይናንስ እርዳታ ምን እንደሆነ፣ ምን ምን

አይነት የፈይናንስ እርዳታ እንደሚገኙ እና ተማሪዎች እንዴት አድርገው በችግር-ለተመሰረተ የፋይናንስ እርዳታ ማመልከት እንደሚችሉ ይማራሉ። ለተጨማሪ መረጃ ከልጅዎ ት/ቤት ጋር ይገናኙ።

**የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሥራ ማስኬጃ ባጀት ለማዘጋጀት የሚጠቅም አስተያየትዎን ይፈልጋል**

በሚቀጥለው የሥራ ማስኬጃ ባጀት በምን ላይ ቅድሚያ ትኩረት መስጠት እንደሚያስፈልግ የእርስዎን ሃሳብ/አስተያየት ዲስትሪክቱ እንዲያውቀው ያድርጉ።

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ለበጀት ዓመት 2020 የሥራ ማስኬጃ ባጀት ዲስትሪክቱ ማተኮር ያለባቸውን አቅጣጫዎች ግልጽ አስተያየቶችን ለማግኘት ይፈልጋል። ለሁሉም ተማሪዎች ውጤቶችን ለማሻሻል ለማገዝ የትኞቹ ስልቶች/ስትራተጂዎች፣ ፕሮግራሞች ወይም ጥረቶች ጠቃሚ መሆናቸውን ወይም የማይጠቅሙ መሆናቸውን ይንገሩን። የተማሪዎችን ውጤታማነት ለማሻሻል የሚያስችሉ አዳዲስ ስልቶችን/ስትራተጂዎችን፣ ፕሮግራሞችን ወይም ጥረቶችን መለየት፣

የእርስዎን ግብረመልስ ለመስጠት እባክዎ ፈጠን ያለ ዳሰሳ /ጥናት ይሙሉ። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ከዚህ ዳሰሳ የሚገኘውን መረጃ/ኢንፎርሜሽን የሚዘጋጀውን ባጀት ለማዳበር ይጠቀማል።

**በአስፈላጊ የቦርድ ፖሊሲ ላይ ግብአት ይስጡ**

ተማሪዎች እስከ ሦስት ቀሪዎችን በዜግነት እንቅስቃሴዎች ላይ ሲሳተፉ በምክንያት እንደቀሩ እንዲቆጠርላቸው የማሻሻያ ሃሳብ በቀረበበት ፖሊሲ/Policy KEA ላይ የትምህርት ቦርድ የእርስዎን አስተያየ ለመስማት ይፈልጋል።

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ በረቂቅ ፖሊሲ/Policy KEA ላይ የህዝብ አስተያየት እንዲሰጥበት ይፈልጋል፣የፖለቲካ ዘመቻ እና ፖለቲካዊ ቁሳቁሶች(KEA)፣ እና የፖሊሲውን ስም መለወጥየዜግነት ተሳትፎ፣ የፖለቲካ ዘመቻ፣ እና ፖለቲካዊ ቁሳቁሶች። የተሻሻለው እና እንደገና ስያሜ የተሰጠው ፖሊሲ ተማሪዎች በዜግነት እንቅስቃሴዎች ላይ ለመሣተፍ እንዲችሉ በምክንያት መቅረት እንደሆነ እሳቤ እንዲኖር የቦርዱን ፍላጎት ያንፀባርቃል።

በ 2017-2018 የትምህርት ዓመት፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች አገራችንን በተገዳደሯት እና በጣም አስፈላጊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ተሳትፈዋል፤ እንዲያውም አገራዊ እውቅና ተስጥቷቸዋል። በአንፃሩም፣ ተማሪዎች ት/ቤት የመከታተል አቋም በማይነካባቸው ሁኔታ በዜግነት እንቅስቃሴዎች ላይ መሣተፍ እንዳለባቸው ተማሪዎች፣ ቤተሰቦች፣

እና የቦርድ አባላት ፍላጎታቸውንና ድጋፋቸውን ገልፀዋል። በአሁን ወቅት፣ ፖሊሲ/Policy KEA ከ9 - 12 ክፍል የሚገኙ ተማሪዎች ከፖለቲካ ተወዳዳሪ ወይም ድርጅት ሲጠየቅ ከወላጅ/ሞግዚት በጽሑፍ ስምምነታቸውን ሲገልጹና ርእሰ መምህር/ተወካይ ካጸደቀ/ች፣ ከፕራይመሪ የምርጫ ወቅት አስቀድሞ ሁለት-ሣምንት በፖለቲካ እንቅስቃሴዎች በትምህርት ሠዓታቸው ለመሣተፍ እንደሚችሉ ይፈቅዳል።

እዚህ የበለጠ ያንብቡ።

ስለዚህ ፖሊሲ ከህዝብ የሚሰጥ አስተያየት እስከ ዓርብ፣ ኦክቶበር 12/2018 ለ30 ቀን የተወሰነ ነው።

የተሻሻለ ፖሊሲ/Revised Policy KEA ያንብቡ

በተሻሻለው ፖሊሲ/Revised Policy KEA ላይ የሚሰጥ አስተያየት

**የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ማመልከቻ ፕሮግራሞች ከኦክቶበር 1 ጀምሮ Parent Portal ላይ ይገኛል**

ወላጆች ለሚቀጥለው የትምህርት ዓመት ስለልጆቻቸው የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ምርጫ በድረ-ገጽ ፓረንት ፖርታል/online parent portal ለማገናዘብ ይችላሉ።

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ወላጆች ለሚቀጥለው የትምህርት ዓመት ስለልጆቻቸው የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ምርጫ ማገናዘቢያ አመቺ የሆነ መንገድ እየሰጠ ነው።

በተማሪዎች የአካባቢ ት/ቤቶች ያሉት ተለይተዉ ከተቀረጹ፣ እና የዳበሩ/የበለፀጉ እና የተፋጠኑ/ከፍ ያሉ ኮርሶች እና መርሃ ግብሮች/ፕሮግራሞች በተጨማሪ፣ ከ 8 ኛ -11 ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ፕሮግራሞች ማመልከቻ ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።

ከሰኞ፣ ኦክቶበር 1 ጀምሮ፣ የተማሪዎች ወላጆች ስለ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ማመልከቻ ፕሮግራሞች በ myMCPS parent portal ላይ ለማግኘት ይችላሉ።

ኦክቶበር 1 ላይ፣ ወላጆች እና ሞግዚቶች ፖርታል ላይ/portal ሊመዘገቡ ይችላሉ፣ በስተግራ በኩል "document library" ወደሚለው ይሂዱና "My Student's High School Application Program Options for 2019-2020" የሚለውን ሪፖርት ያንብቡ። ሊያመለክቱ ለተዘጋጁት እያንዳንዱ ፕሮግራም አጭር መግለጫ፣ የፕሮግራሙ ድረ-ገጽ አድራሻ እና ማመልከቻው የሚገኝበት አድራሻ ይኖራል። ሁሉም ፕሮግራሞች ብቁ ለመሆን የተለያየ

ተፈላጊ መመዘኛ ይኖራቸዋል። የእርስዎ ልጅ አድራሻ፣ የክፍል ደረጃ፣ እና አሁን የሚማርበት/የምትማርበት ት/ቤት ብቁ የመሆን/ያለመሆንን ሁኔታ ይወስን ይሆናል፤ ስለዚህ የእርስዎ ት/ቤት አድራሻዎ እንዳለው እርግጠኛ መሆን አለብዎት።

**የማመልከቻ ማብቂያዉ ቀነ ገደብ ዓርብ ኖቬምበር 2 ነዉ።**

parent portal ለማግኘት እንዲችሉ እርዳታ የሚያስፈልግዎት ከሆነ፣ የእርስዎ ልጅ አሁን ያለ(ች)በትን ት/ቤት ይጠይቁ።

ተጨማሪ መረጃ

**የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሂስፓኒክ/ላቲኖ ቅርስ/Hispanic/Latino Heritage ወርን ያከብራል**

በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ወሩን በሙሉ ለመላው ሀገሪቱ እና ለህብረተሰቡ ስላበረከቱት መልካም አስተዋጾ የሂስፓኒክ አሜሪካኖችን ትውልድ አክብሮት ይዘከራል።

አሊሲያ ዲንይ/Alicia Deeny የታኮማ ፓርክ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት (Takoma Park Middle School) ርእሰ መምህርት በሜሪላንድ ሂስፓኒክ ጋላ/Maryland Hispanic Gala የዓመቱ ምርጥ አስተማሪ“Educator of the Year” በመሆን ሴፐቴምበር 13 ተሰይማለች። አገራዊውን የሂስፓኒክ ቅርስ-ውርስ የጀመረው "The gala" National Hispanic Heritage ወጣቶች ስኬታማ እንዲሆኑ ቁርጠኝነት ያላቸውን ድርጅቶች ያሰባስባል። ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተመርቀው በሜሪላንድ ኮሌጆች እና ዩንቨርስቲዎች ለሚማሩ 55 ተማሪዎች ከ $100,000 ዶላር በላይ ስኮላርሽፕ ተሰጥቷቸዋል።

MCPS Moment video የሚለውን ቪዲዮ እዚህ ይመልከቱ።

ከሴፕቴምበር 15 እስከ ኦክቶበር 15 ያለው ጊዜ የሂስፓኒክ ቅርስ/Hispanic Heritage የሚዘከርበት ወር እንዲሆን የትምህርት ቦርድ አውጇል። የትውልድ ሃረጋቸው ከስፔይን/Spain እና ሌሎች ሰሜን አሜሪካ/North America፣ ሴንትራል አሜሪካ /Central America፣ ሳውዝ አሜሪካ/South America እና ካሬቢያን/Caribbean ስፓንሽኛ ተናጋሪ ከሆኑ አገሮች የተማሪዎች፣ የመምህራን፣ የሠራተኞች፣ እና የማህበረሰቡ ልዩ ባህል እና ልማዶቻቸው ወሩን በሙሉ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች ይከበራል/ይዘከራል።

32 ፐርሰንት የተማሪ ቁጥር፣ እና 21 ስፓንሽ ተናጋሪ አገሮችን በመወከል በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሂስፓኒክ እና ላቲኖ ህብረተሰብ በፍጥነት እያደጉ ያሉ ማህበረሰቦች ናቸው።

በ "Hispanic Heritage Month" ወደፊት ስለሚካሄዱት ሁነቶች/ዝግጅቶች የበለጠ መረጃ/ኢንፎርሜሽን እና በአካባቢዎ ስለሚካሄዱ ዝግጅቶች ዝርዝር እዚህ ያገኛሉ እና ትምህርታዊ መገልገያዎችን ለማግኘት የልጅዎን ት/ቤት በቀጥታ ይጠይቁ/ያነጋግሩ።